የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

Purpose Black ETHIOPIA

2015 ሚያዚያ ቅጽ 1 ቁጥር 8

## የፐርፐዝብላክን የባለአክሲዮንነት ቅደመ ሁኔታዎች ላሟሉ ኢንቨስተሮች የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ የመስጠት ሥራው ተጠናክሮ መቀጠሉን የኩባንያው የባለአክሲዮኖች ጉዳይ(investor relation) ክፍል አስታወቀ።

ፐርፐዝብላክ በመደበኛ፣ በኅብረና ፍራንቻይዝ፣ እና በኅብረና ማቀነባበሪያ ፍራንቻይዝ ሥርዓት ያዘጋጃቸውን አክሲዮኖች ለገዙ እና አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው ለተገኙ ባለአክሲዮኖች የባለአክሲዮንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በዲጂታል መንገድ በማዘጋጀት ተደራሽ እያደረገ መሆኑን የባለአክሲዮኖች ጉዳይ(investor relation) ክፍል ዳይሬክተር ወ/ሮ አዲስዓለም ሳህሉ አስታውቀዋል።

በመደበኛው የአክሲዮን ሥርዓት ተመዝግበው አስቀድመው የኩባንያው መመሪያ የሚደነግገውን ቅድመ ክፍያ ለፈጸሙ ባለአክሲዮኖች በተቀመጠው የሁለት ዓመት ገደብ ውስጥ ቀሪ ክፍያቸውን አጠቃልለው ሲከፍሉ እና ሙሉ ክፍያ መክፈላቸው ሲረጋገጥ ዲጂታል መሆን መንገድ ሕጋዊ ባለአክሲዮንነታቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት እንደሚዘጋጅላቸው የገለጹት ዳይሬክተሯ የምስክር ወረቀቱ ከተዘጋጀ በኋላ ባለአክሲዮኖቹ ባስመዘገቡት የስልክ አድራሻ ተደውሎ በአካል በፐርፐዝብላክ ቢሮ ተገኝተው መውሰድ ከቻሉ ማንነታቸውን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ ወይም መንጃ ፈቃድ ይዘው እንዲመጡ ወይም በውክልና የሚወስዱም ከሆነ ተወካዩ ሕጋዊ በውልና ማስረጃ የጸደቀ ውክልና ይዘው በመምጣት የምስክር ወረቀቱን እንዲወስዱ የማሳወቅ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።





“

**ከመደበኛው አክሲዮን ባሻገር በተለያዩ ምክንያቶች የምስክር ወረቀት ያልወሰዱ የግብርና እና የግብርና ማቀነባበሪያ ፍራንቻይዝ ባለአክሲዮኖች የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶላቸው ባላቸው አድራሻ መጥተው እንዲወስዱ የማሳወቅ ተግባር እየተከናወነ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን ባለአክሲኖቹ ሕጋዊ ማንነታቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ወይም ተወካዮቻቸው ከውልና ማስረጃ የጸደቀላቸውን ውክልና ይዘው በፐርፐዝብላክ ዋና ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ የምስክር ወረቀቱን እንዲወስዱ እንደሚደረግ ወ/ሮ አዲስዓለም ተናግረዋል።**

ቀደም ሲል በእጅ ጽሕፈት (calligraphy) ይከናወን የነበረው የምስክር ወረቀት ዝግጅት የተለያዩ ተግዳሮቶች እንደነበሩት አውስተው አሁን ላይ ክፍሉ ከኩባንያው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ክፍል ጋር በመተባበር ባበለጸገው የዲጂታል ምዝገባ ሥርዓት መተካቱን እና ይህም ጥራቱን በጠበቀ መልኩ እና በተቀላጠፈ አሠራር የምስክር ወረቀቶቹን ለማዘጋጀት ምቹ ከባቢ መፍጠሩን ነው ዳይሬክተሯ የገለጹት።

በተጨማሪም በውጪ አገራት ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የፐርፐዝብላክ ኢቲኤች ባለአክሲዮኖች በተለያየ አጋጣሚ ወደ አገር ቤት ተመልሰው የባለአክሲዮንነታቸውን የምስክር ወረቀት ለመውሰድ ወደ ኩባንያው ሲመጡም ሆነ ሕጋዊ ወኪሎቻቸውን ሲልኩ የምስክር ወረቀት ዝግጅቱ በፍጥነት እየተከናወነ እየተሰጣቸው እንደሆነም የኢንቨስተር ሪሌሽን ክፍል ዳይሬክተሯ ተናግረዋል።

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በገበያ ተኮር ኩታ ገጠም እርሻ ፕሮጀክቱ ቀዳሚ የሆነውን የማስጀመሪያ መርሐ ግብር በሲዳማ ክልል ብላቴ ወረዳ አካሔደ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በሲዳማ ክልል ያደራጃቸውን 3 ክላስተሮች ሚያዚያ 17 ቀን 2015 ባደረገው የመስክ ጉብኝትና ማስጀመሪያ መርሐግብር በይፋ ወደሥራ ማስገባቱ ተገለጸ። በመርሐግብሩ የፐርፐዝብላክ ኢቲኤች ዋና ስራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱን ጨምሮ የተለያዩ የኩባንያው የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም የሲዳማ ክልል የግብርና ተወካይ፣ የብላቴ ወረዳ አስተዳደር እና የዞን ኃላፊዎች ተገኝተዋል።





“

**በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች በኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴ በሚያለማቸው እርሻዎች አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ጥራጥሬዎችን በስፋት እያመረተ የሚገኘው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር በግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ዕቅዱ መሠረት በአማራ ክልል 2፣ በሲዳማ ክልል 3 ክላስተሮችን ወደ ሥራ ማስገባቱን የፐርፐዝብላክ ቺፍ ቴክኒካል ኦፕሬሽን ኦፊሰር አቶ አስናቀ ኀ/ሚካኤል አስተውቀዋል።**



“

**በማስጀመሪያ መርሐግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የTCTዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ክልሎች 17 ክላስተሮች መቋቋማቸውን ጠቁመው በክፍሉ ባጠቃላይ በመላው አገሪቱ የሚገኙ 1 ሚሊዮን ገበሬዎችን የTCTዝብላክ ባለአክሲዮን ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አስረድተው “የክላስተሮቹ መቋቋም ዘመናዊ የግብርና መሳሪያዎችን በማስተዋወቅ የገበሬዎችን ሕይወት ከማቅለል ባሻገር በዕውቀትና በክህሎት በማነጽ የተሻለ ገቢ አግኝተው ዘመናዊ ኑሮ እንዲኖሩ ያስችላልም ብለዋል።**

በዕለቱ በመርሐግብሩ ላይ የተሳተፉ አርሶአደሮች፣ የኩባንያው የሥራ ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት በተቋቋሙት 3 ክላስተሮች በመልማት ላይ ያሉትን እርሻዎች በመጎብኘት የመስክ ምልከታ ያደረጉ ሲሆን ተስፋ ሰጪ የሥራ ውጤቶችን መመልከታቸውን ከክላስተሩ ምስረታ መርሐግብር በኋላ ገልጸዋል።



“

**የTCTዝብላክ ቺፍ ቴክኒካል ኦፕሬሽን ኦፊሰር አቶ አሰናቀ ኀ/ሚካኤል በእርሻዎቹ ላይ በዋናነት የበቆሎ ምርት የሚዘራ ሲሆን በተጨማሪም በቀጣይ አትክልትና ፍራፍሬዎች የሚመረቱ መሆኑን ይፋ አድርገው ገበሬዎቹ የኩባንያውን አክሲዮኖች ሲገዙ ከኢንቨስትመንቶች ትርፍ ተካፋይ ከመሆናቸው ባሻገር በከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር የታቀዱ የዘመናዊ መስኖ ልማት፣ ኢንሹራንስ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተናግረዋል።**

ኃላፊው በፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የግብርናና የግብርና ማስፋፊያ ክፍሎች እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትልቅ መሣሪያ መሆናቸውን አክለው በቀጣይም በሌሎች አካባቢዎች በከብትና ዶሮ እርባታ፣ በአሳና ወተት ምርት እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች ገበያ መር የክላስተር ግብርና ሥራዎች እንደሚከናወኑ አንስተዋል።

የፐርፐዝብላክ ግብርና ክፍል ኃላፊ የሆኑት አቶ እሸቱ ጴጥሮስ በበኩላቸው በክልሉ በክላስተር የተዋቀሩ የግብርና ጽ/ቤቶች መመስረታቸውን አስታውሰው የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማም ገበሬዎችን የፐርፐዝብላክ ባለአክሲዮን በማድረግ የግብርና ዘርፉን ሜካናይዝድ ለማድረግ በሚሠሩ ሥራዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑና ምርትና ምርታማነትን እንዲያሳድጉ ነው ብለዋል።

ክላስተሮቹ ወደ ሥራ ሲገቡም ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የወረዳና ዞን ኃላፊዎችን በመቅጠር በቋሚነት የመሥራት ሒደቱ በኃላፊነት ይከናወናል ያሉ ሲሆን በአካባቢው የሚገኘውንና ዓመቱን ሙሉ የሚፈስሰውን የብላቴን ወንዝ በመጠቀም የሚገነቡ የመስኖ ልማቶች፣ የግብርና ግብአትና ማሽነሪዎች አቅርቦት፣ ኢንሹራንስ እንዲሁም ክምችትና የገበያ ሰንሰለት ማዕቀፉን የማመቻቸት ኃላፊነቶች በኩባንያው እንደሚከናወኑ ጠቁመው አርሶአደሮች ምርቶቻቸውን የሚረከባቸው እንዳያጡና ምርት እንዳይባክን በአገር ውስጥና በውጪ ገበያዎች የግብይት ትስስር የሚፈጥሩበት አሠራር መዘርጋቱን አስታውቀዋል።

የፕሮጀክቱንም ውጤታማነት እውን ለማድረግ በአርሶአደሮች በኩል በእርሻው ላይ የሚሠሩ ሰዎችን የማግኘትና አርሶ አደሮችም ፐርፐዝብላክ ባቀረበላቸው የአክሲዮን ባለቤትነት ግብዣና የክላስተሮች መቋቋም ከፍተኛ ፍላጎት እያሳዩ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን ከ3ቱ ክላስተሮች በአንዱ በተጀመረው እንቅስቃሴ ትራክተሮችን በመከራየት የእርሻ ሥራዎችን ማስጀመር መቻሉ ተገልጿል። በቀጣይም የምርጥ ዘርና ማዳበሪያ እንዲሁም ኬሚካሎች አቅርቦት በጥራትና በብዛት ለአርሶ አደሩ ይደርሳል ተብሏል።

## 9 የአፍሪካ አገራት ከTCTዝብላክ ግሎባል ጋር በአጋርነት ለመሥራት ፍላጎት ማሳየታቸው ተገለጸ።

“

**በመላው ዓለም በኢኮኖሚ የዳበረ፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ እና የተከበረ ጥቁር ማኅበረሰብ መፍጠርን ተልእኮው አድርጎ በተግባር ላይ የሚገኘው TCTዝብላክ ግሎባል የTCTዝብላክ አፍሪካ ተነሣሽነትን በሁሉም የአህጉሪቱ አገራት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን ተከትሎ በTCTዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ሰብሳቢነት ቻድ፣ ጋና፣ ቤኒን፣ ጊኒ፣ ካሜሩን እና ታንዛንያን ጨምሮ ከ7 በላይ የአፍሪካ አገራት ተወካዮች ጋር የበይነ መረብ ስብሰባ መደረጉን የTCTዝብላክ ኢትዮጵያ የአፍሪካ እንቅስቃሴ ኀላፊ አቶ ኢዮብ ዳንኤል አስታውቀዋል።**

በተለያዩ የኩባንያው ባለድርሻ አካላት ጋባዥነት ከተገኙት የየአገራቱ ተወካዮች በተጨማሪም የከገበሬው ኢ-ኮሜርስ ዳይሬክተርን ጨምሮ ሌሎችም የሥራ ኃላፊዎች በስብሰባው ላይ መገኘታቸው የተገለጸ ሲሆን በውይይቱ ላይ የፐርፐዝብላክ፣ መስራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ሰፋ ያለ ገለጻ አድርገው የፐርፐዝብላክ ግሎባልን አመሰራረት፣ ፐርፐዝ ብላክ ኢትዮጵያ አሁን የደረሰበትን ደረጃ፣ የፐርፐዝብላክ ናይጀሪያን ተሞክሮ እና ሌሎችም ተነሳሽነቱን የተመለከቱ ነጥቦችን በስፋት አንሥተዋል።



“

**ዋና ሥራ አስፈጻሚው በቅርቡ ከናይጄሪያ እና ሶማሊላንድ ተወካዮች ጋር በመወያየት እየተሠሩ ያሉ የቅርንጫፍ ቢሮዎችን የመክፈት ቅድመ ዝግጅቶችን አውስተው “የተነሣሽነቱን ራዕይ በመጋራት ሁሉም አፍሪካ ሃገራት ዜጎች ያላቸውን የተፈጥሮ ሃብት፣ የገንዘብ እና ሌሎችም አቅሞቻቸውን በማቀናጀት ኢኮኖሚያዊ ብቃታቸውን ሊገነቡ ይገባልም” ብለዋል።**

ዶ/ር ፍስሐ አክለውም በኢትዮጵያ ተግባራዊ ማድረግ እንደተቻለው የአፍሪካ አህጉር ዋና የኢኮኖሚ ምንጭ በሆነው ግብርና ላይ ትኩረት በማድረግ የገበሬዎችን ሕይወት ከመለወጥ፣ በአህጉራዊ ቀጠናው የጨመረውን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ከማቅለል ባሻገር በሚገነቡት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ስለሚቻል በኢኮኖሚ የዳበረ ማኅበረሰብን ከመፍጠር አኳያ ተነሳሽነቱ የሚኖረው ሚና ጉልህ ነው ሲሉም ስለ አዋጭነቱ ያስረዳሉ።

እንደዋና ሥራ አስፈጻሚው ንግግር በሁሉም ሃገራት የሚቋቋመው የፐርፐዝብላክ ቢሮ እንደ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሁሉ በየአገራቱ ስያሜ በራሳቸው ዜጎች መስራችነት የሚቋቋም ሲሆን ይህም ከሌሎች እርዳታና ጣልቃ ገብነት በጸዳ መልኩ የራስን ኢኮኖሚያዊ አቅም ከማጠናከር አኳያ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ይኖረዋልም ተብሏል።

በመጨረሻም ሁሉም ሃገራት የስኬትና የልዕልና ታሪካቸውን በጋራ ሊጽፉ እንደሚገባ የተነገረ ሲሆን እንቅስቃሴው በአገራቱ መካከል በአህጉር አቀፍ ደረጃ ጠንካራ የንግድ ትስስርን እና የጠበቀ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን በመፍጠር ረገድ አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንደሚኖረውም ተገልጿል።

የአገራቱ ተወካዮችም ፐርፐዝብላክ ግሎባል 55ቱንም የአፍሪካ አገሮች በአንድ ለማገበያየት የተወጠነውን አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና ጉዳይ እውን ለማድረግ ትልቅ መሣሪያ እንደሚሆን አጽንዖት በመስጠት ከዚህ ተጽዕኖ ፈጣሪ ተነሳሽነት ጋር በጥምረት ለመሥራት ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልጸዋል።

**ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት ሲስተም ለሚያደርገው የበይነ መረብ ግብይት ከሎጂስቲክስ ኩባንያዎች ጋር የአጋርነት ሥራዎች መጀመራቸው ተገለጸ።**

ምርት ለክፍለ ሃገር እና ምርት ለዲያስፖራው በሚሉ ተነሣሽነቶች ምርቶችን ለደንበኞች ለማቅረብ እየሠራ የሚገኘው የፐርፐዝብላክ ኢ-ኮሜርስ ክፍል ከተለያዩ አምራቾች የሚገኙ ፍጆታዎችን በከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት ሲስተም የግብይት መድረክ አማካኝነት ለተጠቃሚዎች የማከፋፈል(delivery) አገልግሎት ሊሰጡ ከሚችሉ ተቋማት ጋር መወያየቱን የኢኮሜርስ ዳይሬክተር አቶ አማኑኤል መለሰ አስታወቁ።

ከፐርፐዝብላክ የግብርና ምርቶች እና የማቀነባበሪያ ውጤቶች በተጨማሪ ምርትና አገልግሎት አቅራቢዎች፣ አምራቾች እና ገዢዎች በአንድ ቦታ የሚገበያዩበት የበይነ መረብ ሥርዓት የሆነው ከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት ሲስተም ከአስቤዛና መድኃኒቶች ጀምሮ እስከ አልባሳት እና ማሽነሪዎች ያሉ ምርቶችን በመላ አገሪቱ ብሎም በዓለም ዙሪያ ለገበያ የሚቀርቡበት የግብይት መድረክ መሆኑም ተገልጿል።

በተነሳሽነቱ የተጀመሩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በተመለከተም ከተለያዩ ምርት አከፋፋይ ድርጅቶች ጋር ተገናኝተው መነጋገራቸውን ያብራሩት ዳይሬክተሩ "25 ከሚደርሱ በአሜሪካና ካናዳ የሚገኙ ሱፐርማርኬቶች ጋር በጥምረት ለመሥራት የሚያስችሉ መንገዶች እየተመቻቹ ነው” ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

ምርት ለክፍለሃገርን በተመለከተም “እንደማስጀመሪያ አዳማ፣ ባሕር ዳር፣ ድሬዳዋ፣ ሃዋሳ፣ ጅማና በዙሪያቸው የሚገኙ ከተሞችን የሚያሳትፍ የሙከራ ፕሮጀክት በቅርቡ ተግባራዊ ይደረጋል ሲሉ አቶ አማኑኤል አክለዋል።

በመጨረሻም ዳይሬክተሩ የመገበያያ ድረ ገጹን ወደተግባር ለማስገባት ምርትና አገልግሎት አቅራቢዎች የሚስተናገዱበትና የክፍያ ሁኔታን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን ያካተተ ሕጋዊ ሰነድ ተጠናቅቆ ከገበሬው ቬንደር ማኔጅመንት በቅርቡ ወደ ሥራ እንደሚገባ አስረድተው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያም ከገበሬው ምርቶች ባሻገር እንደየ እቃዎቹ ዋጋና ሁኔታ ከ2–15% በሚደርስ አገልግሎት ክፍያ የግብርና፣ የማቀነባበሪያ፣ የእደ ጥበብና ሌሎች ምርቶች በአንድ የበይነ መረብ ግብይት ለተጠቃሚዎች የሚያደርስ በመሆኑ በየትኛውም የአገሪቱ እና የዓለም ክፍል ያሉ አምራቾች ምርትና አገልግሎታቸውን በስፋት ተደራሽ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል ሲሉ አብራርተዋል።

ከገበሬው FARMER


**ዋና አዘጋጅ፦ ሰላማዊት ደበበ**
**ሲንየር ሪፖርተር፦ ጌታባለው ገ/ሐና**
**ሪፖርተር፦ ኤደን ደነቀ**



**ለበለጠ መረጃ**

ሰንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ

+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222

7151

www.purposeblackethiopia.com